# ለአገር ሠላምና ልማት ሕገ-መንግሥታዊ አሰራርን ማጠናከር

ገብረሚካኤል አስገዶም 04-23-18

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርና ካቢኔያቸው በርካታ ሥራዎች ይጠብቋቸዋል፡፡ ሕዝብም ብዙ ነገር ይጠብቃል፡፡ ባገኙት አጋጣሚ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማከናወን ስላለባቸው ጉዳዮች በመዘርዘር ሐሳብ የሚያቀርቡ አሉ፤ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን እዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባው ማሳሰቢያዎቹ ኃላፊነት የተሞላባቸው እንዲሆኑ ነው፡፡ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚቀርቡ ማሳሰቢያዎች የኢትዮጵያን አስቸጋሪና ውስብስብ ፖለቲካ ያመዛዘኑና የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ሕዝብን ማዕከል ያደረጉ፤ አንገብጋቢ የሚባሉ አጣዳፊ ጉዳዮች ቅድሚያ ቢያገኙ ተመራጭ ነው፡፡

በሒደት ደግሞ በቅደም ተከተል የሚፈቱ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ማጤንም ተገቢ ነው፡፡ ከጠባብ ግላዊና ቡድናዊ ፍላጎቶች በመላቀቅ አገሪቱን ከገባችበት ቀውስ ለማውጣት የሚረዱ የመፍትሔ ሐሳቦች መቅረብ አለባቸው፡፡ በፖለቲካ ቀውሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች መልሰው እንዲቋቋሙ፣ ከፍተኛ እክል ያጋጠመው ኢኮኖሚ እንዲያገግም፣ ለዓመታት የተዘጋው የፖለቲካ ምኅዳር እንዲከፈት፣ ከእስር መለቀቅ ያለባቸው ዜጎች እንዲፈቱ፣ ነፃ የሐሳብ ልውውጦችና ውይይቶች በስፋት እንዲጀመሩ፣ ወዘተ. በጎ ሆኖ መቅረብ ተገቢ ነው፡፡ ከክፋት የሚገኘው ጥፋት ብቻ ነው፡፡

አገሪቱን ወደ ተረጋጋ ሰላምና ልማት መንገድ መመለስ የሚቻለው ደግሞ ህጋዊ አሰራርን በመከተል በተለይም ህገ-መንግስቱ የሚደነግገውን አሰራር  ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ከአሁኑ ህገ-መንግስት ተቃራኒ በሆነ መንገድ ከዚህ ቀደም የነበሩት የደርግና አፄያዊ የአሰራር ሥርዓቶች ይገዙና ያስተዳድሩ የነበረው በማስገደድና ከሕዝብ ፍላጎት ውጪ ጫና በመፍጠር ነበር፡፡

በ1987 ዓ.ም የፀደቀው ሕገ-መንግሥት  ለልማትና ለዴሞክራሲ በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በአግባቡ እንዲከበሩ እንዲሁም መንግሥት ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ እንዲሆን የሚያስገድድ ሕገ መንግሥት ነው፡፡ የቡድን መብቶች በሕገ መንግሥቱ በመታወጃቸው ሕገ-መንግሥቱ ለግል መብቶች ቦታ ያልሰጠ ተደርጎ የሚነሳው ትችት ከእውነታ የራቀ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ሕገ-መንግሥቱ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ከመያዙ ባሻገር ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ላይ በተቀመጠው መሰረት አንድም ሳያስቀር ልቅም አድርጎ  የያዘ ነው፡፡

አገራችንን አሁን ያጋጠማትን የሰላምና ቁልቁል ለመንደርደር የማሰብ አዝማሚያ በፍጥነት ለመፍታት ሕገ-መንግሥታዊ አሰራርን በማስፈንና የሕግ የበላይነትን በማስከበር ሰላምና መረጋጋትን ማጠናከር ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለዚህ ደግሞ መነሻና ጠንካራ መደላድል መሆን የሚችል እንዲሁም አገራዊ አንድነትና ተስፋ በውስጡ የሰነቀ ሕገ-መንግሥትና ሕጋዊ አሰራር ስላለን እነዚህን አብይ የሰላም ምሶሶዎች በማጠናከር ያለምንም ማፈግፈግ ወደ ሰላምና ልማት እንዲሁም ዴሞክራሲ ግንባታና ኢንቬስትመንት ማስፋፋት መገስገስ አስፈላጊ ነው፡፡

ካለፉት ጊዜያት ስንጀምር በኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል የነበረው ጥልቅ ውይይትና የሪፎርም አሰራር ሁኔታ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደ አንድ ጥሩ መነሻ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የቱንም ያህል ውይይትና ክርክር እንዲሁም አለመግባባት ቢኖርም እንኳን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ውሳኔዎች እስከተላለፉ ድረስ ለብዙኃኑ ውሳኔ መገዛት፤ ውሳኔውንም ማክበርና ተስማምቶ መሥራት እንደ መልካም አጋጣሚ መታየት ይኖርበታል፡፡

በሕገ-መንግሥታችን አንቀጽ 38(3) ላይ እንደተገለጸው የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሁም የማንኛውም ፓርቲ ውስጣዊ አሠራር ጭምር ዴሞክራሲያዊ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል የተካሄዱት ውይይቶች፣ክርክሮችና ተያያዥ ጉዳዮች በብሔሮች መካከል መጠራጠርና ሥጋት የሚያጭሩ አይደሉም፤ሊሆኑም አይገባም፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት የሃሳብ ፍጭት ያለባቸውን ሒደቶች ማለፍ ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታን የመወጣት አካሄድ በመሆኑ ነው፤ ከሐሳብ ልዩነት የሚፈልቁ ውይይቶች፣ክርክሮችና ፍጭቶች በአንድ ፓርቲም ውስጥም ቢሆን ሊከሰቱ የሚችሉ ናቸው፡ አይደለም በብዙ ፓርቲዎች ውስጥ፡፡

በመግቢያው ላይ እንደተበየነው የሕገ-መንግሥቱ ዋና ግብ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር ነው፡፡በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የሠፈሩት አንቀጾችም ግባቸው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሰላም፣በልማትና በዴሞክራሲ ላይ የተመሰረተ እንዲሁም ኢትዮጵያዊ የሆነ አንድ ማኅበረሰብ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ማንኛውም ዜጋ ብሔራዊ ማንነቱን ይዞ በብሔር ማንነቱ ተሰባስቦም የብሔር መብቶቹ ተጠብቀውለት ከሌሎች ብሔሮች ጋር በአንድነት ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብን መገንባት ግድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ወደዚህ ግብ ማድረስ አለበት፡፡ ብሔርን መሠረት ያደረጉ ፓርቲዎች በመኖራቸው የተለያዩ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ክርክርና ውድድር ቢኖርም፣ ውሳኔ ካለፈ ግን ውሳኔውን በፀጋ መቀበል የዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ መገለጫ ነው፡፡

ይህንን አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ሕገ-መንግሥቱ በሚያስቀምጠው አሰራር የዜጎችን የእኩልነት መብት ማክበር አስፈላጊ ነው፡፡ ሕገ-መንግስቱ ሁሉም ዜጎች እኩል ናቸው ሲል ማንነትን መሰረት ያደረገና አድሏዊ አሠራር ተቀባይነት የለውም ማለቱ ነው፡፡ በመሆኑም አንቀጽ 25 ላይ እንደሠፈረው በማንኛውም ዜጋ ላይ

ፖለቲካዊ አመለካከቱን፣ ብሔሩና ብሔረሰቡን መነሻ አድርጎ አድልኦ መፈጸም ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ ገበያዎች ላይ ለሁሉም ዜጎች ዕኩልነትን የሚያሰፍንና ውድድር እስካለ ድረስ ለአብሮነትና በመተሳሰብ ላይ ለተመሰረተ ኢትዮጵያዊነት ምሰሶና ማገር ሆኖ ማገልገሉ አይቀርም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ዜጎች ብሔራቸውን መሰረት ባደረገ ፍርደ-ገምድል አሰራር በመከሰቱ ምክንያት ሲፈናቀሉ እና ከተፈናቀሉም በኋላ ሕገ-መንግሥቱና ሌሎች ሕጎች በሚፈቅዱት መሠረት የማስተካከያና የእርምት ዕርምጃ መውሰድ እስከተቻለ ድረስ ኢትዮጵያዊነት ብዙ ውጣ ውረዶችን (እንዲሁም ከፍታና ዝቅታዎችን) እየተሻገረ ማበቡ አይቀርም፡፡ ከዚህ አንፃር የቡድንና የግለሰብ መብት እርስ በራሳቸው የሚደጋገፉ እንጂ የሚቃረኑ አለመሆናቸውን ማጤን ተገቢ ነው፡፡

ሕገ-መንግስቱ በመግቢያው ላይ እንደሚያትተው በኢትዮጵያ ያለው የሉዓላዊነት መገለጫ በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ላይ የተመሰረተ ይሁን እንጂ ዞሮ ዞሮ ዓላማው አንድ ኢትዮጵያዊ (የፖለቲካ) ማኅበረሰብ መፍጠር እስከሆነ ድረስ ምንም ችግር የለውም፡፡ እንዲያውም ሁሉም ብሔሮችና ብሔረሰቦች እንዲሁም ሕዝቦች በፌዴራል ተቋማት ውስጥ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ውክልናና ተሳትፎ እንዲኖራቸው ዋስትና ይሆናል፡፡

ምንም እንኳን አንዳንድ ዜጎችና ፓርቲዎች ያላቸው አስተሳሰብ ወደ አንድ አቅጣጫ ጽንፍ የወጣ ቢሆንም የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አብዛኛው አንቀፅ የሚያትተው ዜጎች ስላላቸው ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ነው፡፡ አብዛኖቹ አንቀጾችም ከዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች የተቀዱ ናቸው፡፡ከህገ-መንግስቱ በጣም ጥቂት አንቀፆች ብቻ አገራዊ ሁኔታንና አሰራርን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው(ስለብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አርብቶ አደሮች ወዘተ)፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የብሔር ቅርፅ የነበራቸው ችግሮችና ሥጋቶችም መከሰታቸው ይታወቃል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ተግዳሮቶችና ሥጋቶች አብሮነታችንን፣ ወንድማማችነታችንና እህትማማችነታችንን የሚፈታተኑ “እኛና እነሱ” የሚያባብል ብሎም ማለቂያ ወደሌለው አዘቅት የሚወስዱ ናቸው፡፡በመሆኑም ለአገራዊ ሰላምና አንድነት ሲባል እንደዚህ አይነት አካሄዶች በእንጭጭ መቀጨት ይኖርባቸዋል፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች ችግሮቻችንን ለመፍታት የሚያስችል ሆኖ ቢቀረፅም ሕገ-መንግሥቱ ለዜጎች የሰጠውን ክብር፣ ዋስትናና ጥበቃ በትክክል መተግበር አልተቻለም፤ካልሆነም በብሔር ጋርደነዋል፡፡

የኢኮኖሚ መብቶችንና ጉዳዮችን አስመልክቶ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 32 እና 41(1) ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ብሔሩ ምንም ይሁን ምን፣ ገደብ በሌለው ሁኔታ በየትኛውም የአገሪቱ

ክፍል ተዘዋውሮ፣ በማንኛውም የኢኮኖሚ መስክ ተሠማርቶ ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው፡፡ እነዚህ መብቶች በክልል ሕገ-መንግሥታት በድጋሚ ተረጋግጠዋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ መብቶች በሌሎች እንዳይጣሱ የማስከበር ግዴታ ያለበት መንግሥት ነው፡፡ መብታቸው ሲጣስ ግለሰቦቹም የመክሰስ መብት አላቸው፡፡ የመንቀሳቀስ መብት ሲጣስ ወይም እክል ሲፈጠር፣ በተጨማሪም ከተሠማሩበት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ እንቅፋት የሆኑ ሰዎችን ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ በፍርድ ቤት ማስወሰን ይቻላል፡፡

ግለሰቦች መብታቸውን ለቡድኖች ጥቅም፣ በቁጥር ብዙ ስለሆኑ አሳልፈው መስጠት አለባቸው የሚል በእኛም ሕገ-መንግሥት ይሁን በሌሎች ላይ የለም፡፡ የቡድን መብት መሠረቱም የግለሰብ መብት ነው፡፡ የግለሰቦች መብት እየተጣሰ የቡድን መብት ሊከበርም አይችልም፡፡ ለነገሩ የኢሕአዴግ ይፋዊ አቋምም ይሄንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

ፓርቲው አቋሙን "በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች" እንደተገለጸው ሕገ መንግሥቱ የግለሰቦችን መብት በማስከበር ሽፋን የብሔር ብሔረሰቦች መብት መረገጥን እንደማይቀበል ሁሉ በብሔር/ብሔረሰቦች መብት መከበር ሽፋን የግለሰቦች መብት መታፈንን እንደማይቀበል ይገልጻል፡፡

ሕገ-መንግሥቱ ላይ እንደሠፈረው የዜጎችን መብት አለማክበርም አለማስከበርም በዜጎች መካከል ልዩነት ይፈጥራል፤ ‹‹ከሌሎች ክልሎች ለስራ ፍለጋ የተንቀሳቀሱ ዜጎች ከአካባቢው ተወላጆች ጋር በእኩልነት እንዳይታዩ ያደርጋል፡፡ ዜጎች በአገራቸው በእኩልነት የመመረጥ መብታቸውን እንዳይተገብሩ እንቅፋት ይሆናል፣ እንዲህ ዓይነት መብቶችን ለመጠቀም ዜጎች የግድ ወደ መጡበት ክልላቸው መሄድ አለባቸው ያሰኛል፡፡

ከዚህ ባለፈ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የትም ይኑር የትም፣ ቋንቋው የፈለገውን ቢሆን መራጩ እስከመረጠውና እስከፈለገው ድረስ የመመረጥ መብት አለው፡፡ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 እና 38 መንፈስ ይህ ነው፡፡ የማንኛውንም የብሔር አባላት ያለ አድልኦ መራጩ እስከፈለገና ጥቅማችንን ያስጠብቅልናል እስካሉ ድረስ የፈለጉትን መምረጥ የእነሱው ኃላፊነት ነው፡፡

አገራችን ውስጥ ለተከሰቱት ችግሮች ፈጣሪያቸው ያው እኛው ኢትዮጵያውያን ነን የምናስተካክላቸውም ራሳችን ነን፡፡ ለማስተካከልም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በመተግበር ቀጥሎም የሚሻሻሉትን በማሻሻል ሊሆን ይችላል፡፡ እስካሁን የተፈጠሩት ችግሮች በዋናነት ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን በአግባቡ ሥራ ላይ ባለማዋል የመነጩ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት የተፈጠሩ ችግሮች ቢኖሩም፣ ሕገ-መንግሥቱን በዕውቀትና በሙሉ ልብ በመተግበር ማስተካከል ይቻላል፡፡ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን በቅን ልቦና ማክበርና ማስከበር እስከቻልን ድረስ ብሔራዊ ማንነታችን ለኢትዮጵያዊነታችን ስንቅና መደላድል እንጂ እንቅፋት ሊሆንብን ከቶም አይችልም፡፡